# ዘመን የማይሽረው ሕያው ታሪክ (እነማን ነበሩ?)

ከሶራ ጃዌ (ስዊስ)

መቻቻል 3ኛ ዓመንታዊት ሮማ ዳግም የታደሰች መስላለች። መንገዶቹ ሁሉ የፊት ማያ መስተዋት መስለዋል። እንዴት አደርሽ ጣሊያን? እንዴት አደርሽ ሮማ? የሚል የጣሊያን ሬዲዮ ድምፅ ይስተጋባል። ሁሉም የክቱን፣ እንዲሁም ደግሞ የማዕረግ ልብሱን በየበኩሉ ለብሶ የኦሊምፒክ ውድድር የመዝጊያውን ቀን ሥነ-ሥርዓት ለማየትና ለመሰናበት ከየቦታው ወደ ሮማ ስታዲየም ይጐርፋል። ይተማልም። ጊዜው እ.ኤ.አ. 1960 ነው። ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ መድረክ ላይ በብስክሌትና በሩጫ ውድድር የተካፈለች ሲሆን፣ የብስክሌት ተወዳዳሪዋ  በውድድሩ ላይ ተጠልፎ ከወደቀበት ተነስቶ 7ኛ ሊወጣ ቻለ። ገረመው ደንቦባ።

የመጨረሻውን እና  ተናፋቂውን ማራቶን ለመጀመር «በስመ-አብ ወወልድ« ብሎ አማትቦ እስኪጨርስ ድረስ እንኳ ፋታ አላገኘም። የውድድሩን መጀመር የሚያበስረው የሽጉጥ ድምፅ አስደነገጠው። እንደ ሽጉጧ ጥይት ተተኩሰው ያፈተለኩትን ከተለያዩ ክፍለ-ዓለማት ከተውጣጡ 79 ወጣት ተወዳዳሪዎች ጋር ተከትሎ ተነሣ። በሕልሙ ይሁን በእውኑ በውል አልታወቀውም። ግን መሮጡን አላቆመም፣ ይሮጣል፣ ይቀድማል፣ ወደፊት ይገሰግሣል... ይሁን እንጂ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ነበር ውድድሩ ላይ መሆኑን የተገነዘበው። ያውም ማራቶን! 42 ኪሎ ሜትር ከ195 ሜትር ርቀት! ከተወዳዳሪዎቹ መካካል ለየት ያለ ቀለም ያለው አንድ አትሌት ይታያል። ታዲያ ማንም ስለ አንድ አፍሪቃዊ    ብቸኛ ጥቁር አትሌት ቦታ መስጠት ቀርቶ በንቀት መልክ ነበር የሚገላምጡትና የሚሣለቁበት። በውድድሩ መንፈስ ውስጥ ብቻ የነበረው ቆፍጣናው አፍሪቃዊ የኢትዮጵያ ልጅ ከፊት መሪ ተወዳዳሪዎቹ ጋር ፍልሚያ ተያይዟል። ውድድሩን በመቀባበል በየኪሎ ሜትሩ ፍጥነታቸውን በመጨመር እያንዳንዱ ተወዳዳሪ ለሐገሩ ክብር የጭንቀት ውድድር ውስጥ ይገኛል።


ብርቅዬውና ውዱ የኢትዮጵያ ልጅ አበበ ቢቂላ ከእነዚህ ተወዳዳሪዎች አንዱ ነው። ውድድሩ ከተጀመረ 20 ደቂቃ አልፎታል። አበበ በመሪነት ካሉት መካካል አንዱ ቢሆንም ከተወዳዳሪዎቹ ጋር አብሮ መጓዝ ግን ፈፅሞ አልተዋጠለትም። ተፎካካሪዎቹ ሣያስቡት የፊት መሪነቱን ቦታ ይዞ ፍጥነቱን በመጨመር ውድድሩን ቀጠለ። ማንም ፉጭ በአጠገቡ የለም። ለዓለም ሕዝብና ለመላው የጣሊያን ነዋሪ የሚተላለፈው የዜና ማሰራጫ ለአንድ አፍታ ፀጥ አለ። ውድድሩን የሚያስተላልፈው ጣሊያናዊ ጋዜጠኛም አይኑ ፈጧል። ይንቆራጠጣልም። የደነገጠም የተገረመም ይመስላል። ድንገት ከሕልሙ እንደባነነ ሰው ድምፁን ከፍ በማድረግ መጮህ ጀመረ። «ምን ዓይነት ጉድ ነው! እኔ አላምንም! ይገርማችኋል! ማ ማ ሚ ያ! ይደንቃል!» ይል ጀመር። ንግግሩን በመቀጠል «አንድ ጥቁር አፍሪቃዊ በማይታመን ሁናቴ ውድድሩን ብቻውን፣ የመሪነት ቦታውን እስካሁን በሞኖፖል ተቆጣጥሮታል። ጥቁር አፍሪቃዊ ነው።»  ደጋግሞም የጥቁርነቱን ምልክት ይናገራል፣ ይጮሃል፣ ይለፈልፋልም። ኢትዮጵያዊ መሆኑን ግን በትክክል ያውቃል። እንዳይናገረው አንደበቱን የቆለፈው ታሪክ ግን አለ። ኢትዮጵያ ጣሊያን ባዘጋጀው ኦሊምፒክ ማሸነፍ ማለት ጣሊያን ለሦስተኛ ጊዜ በኢትዮጵያ እንደተሸነፈች ነበር ለጋዜጠኛው የታየው። ሣልሣዊ ውርደት!!

ጋዜጠኛው አሁንም የሬዲዬ መልዕክቱን ማስተላለፉን አላቆመም። «...ማ ማ ሚ ያ! ፍጥነቱን ከልክ በላይ ጨምሯል፣ የድካም ምልክት አይታይበትም፣ ይጨርስ አይጨርስ ግን

በትክክል አላውቅም፤ የሚገርማችሁ ነገር ቢኖር እግዜር እንደፈጠረው ባዶ እግሩን ነው፤ ኢትዮጵያዊ ነው። አቢሲኒያዊ ነው። ይጨርሣል ብዬ አልገምትም ...» ብሎ ያሚርታል። ውድድሩን በጥሞና በመከታተል ላይ የነበሩትና የአበበም አሰልጣኝ እንዲሁም የቡድኑ መሪ ሆነው የሂዱት አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ውስጣቸው ተረብሿል። አንዴ ይቀመጣሉ፤ ሌላ ጊዜ ይነሣሉ... በተመስጥኖ ውጤቱን ይከታተላሉ። በዚህ መካከል አንድ እንግሊዛዊ ጋዜጠኛ በለሰለሰ አንደበትና ሥነ-ሥርዓት ጐንበስ በማለት «አቶ ይድነቃቸው ባልሣሣት እርስዎ ነዎት?« በማለት ሲጠይቃቸው «አዎ ምን ነበር?» በማለት መለሱለት። ጋዜጠኛውም ቀጠል አድርጐ «የእርስዎ ተወዳዳሪ ውድድሩን በከፍተኛ ርቀት በመምራት ላይ ነው። ውጤቱ ምን ይመስለዎታል?» በማለት ሲጠይቃቸው፤ «ለጥያቄህ አመሰግንሃለሁ። ውጤቱን በኋላ አብረን እናየዋለን።» ነበር ያሉት በትህትና።

የውድድሩን ሂደት በጥሞና እየተከታተሉ የሚዘግቡት የተለያዩ አገር ጋዜጠኞችም ቢሆኑ ከጣሊያናዊው ጋዜጠኛ ብዙም ባይለዩም በንግግራቸው፤ በአገላለጣቸውና በአቀራረባቸው ሁሉም የአበበን ሥዕላዊ ድርሰት በየተራ የሚያነቡ ይመስላሉ። የአቤን እጅ አወዛወዝ፤ የእግር አጣጣሉን፤ ቁመናውን፤ አፍሪቃዊነቱን ጥቁርነቱን በመደጋገም ለመግለፅ ይሞክሩ እንጂ የአበበን ውስጣዊ መንፈስና ሞራል-ጠንካራነት ብሎም አይበገሬነት ግን ከርሱ በስተቀር ማንም የተረዳው ሰው አልነበረም።

ውድድሩን በከፍተኛ ፍጥነትና በሙሉ ኃይል እንዲሁም በአስተማማኝ ርቀት የሚመራው አበበ፤ ሮማ ስታዲዮም ሲደርስ ተመልካቹ ሕዝብ ከመቀመጫው ብድግ በማለት ጭብጨባውን አቀለጠለት። ጀግናው ኢትዮጵያዊ አዲስ የኦሊምፒክ ክብረ ወሰን በባዶ እግሩ በመስበር አሸነፈ። ድልን ተቀዳጀ። ድሉ ለኢትዮጵያ ብቻም ሣይሆን ለአፍሪቃም ጭምር ሆነ። በነገራችን ላይ አበበ ውድድሩን እንደቀላል ነበር የጨረሰው። በውጤቱም ቀደም ሲል በሩሲያዊው ሰርጌይ ፖፖቭ በ2፡30፡00 የተያዘውን የሰዓት ሪኮርድ በ2፡16፡02 አሻሻለው። በዚህ በሮሙ ውድድር የተሰለፈው አበበ ዋቅጅራ ደግሞ እግሩ ፈንድቶ በሰርጌይ ፖፖቭ ለጥቂት ተቀድሞ 7ኛ ወጣ። ከርሱ በኋላ ተከታትለው በመግባት ላይ ያሉትም ተራ በተራ ፍንግል እንደያዛት ጫጩት ሜዳ ላይ ተዘርረዋል። በቃሬዛም በድጋፍም የተወሰዱ ነበሩ። አበበ ግን ለውድድሩ እንደሚዘጋጅ ተወዳዳሪ ጂምናስቲክ ይሠራል። አካሉንም ያዝናናል።



አበበ ልዩ ተስጥዎ የነበረው ሞራል-ጠንካራ አትሌት ነበር። ኢትዮጵያ ከሮማ ኦሊምፒክ በፊት በ1956 በሜልቦርን ኦሊምፒክ ተሣትፋ ነበር። ተወዳዳሪ ሆነው የቀረቡት በ100 ሜትር አቶ ንጉሤ ሮባ፤ እንዲሁም በማራቶን ባሻ ተብለው የሚጠሩት ዛሬ

በሕይወት ያሉና የፌዴሬሽኑ ዘበኛ ነበሩ። በውጤቱም ባሻ ውድድሩን ጨርሰዋል። አቶ ንጉሤም አፈሩን ያቅልልላቸውና ውድድሩን ፈፅመዋል።

የዓለም የማራቶን ውድድር ስም ከተነሣ ከሮማ ኦሊምፒክ በፊት በተደረጉት ውድድሮች በርካታ ተወዳዳሪዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል። ብዙዎቹ አቋርጠዋል። በዚያን ዘመን ያሸነፉትም ቢሆኑ ከ3 ሰዓት በላይ ነበር የፈጀባቸው። አበበ ግን በማይታመን ሁናቴ ከላይ በተገለጠው መሠረት አዲስ ሬኮርድ ነው ያስመዘገበው።

አበበ ከሮማ ኦሎምፒክ ሜዳ የአበባ ጉንጉንና የማራቶን የወርቅ ሜዳሊያውን በአንገቱ አስገብቶ ወደ እናት ሐገሩ በደስታ ተመለሰ። የሐገሩ ሕዝብም በጭብጨባ፣ በደስታ፣ በእልልታና በጭፈራ ተቀበለው። በተለይም ደግሞ የክፍሉ የሥራ ባልደረቦች የሆኑት የክብር ዘበኛ ጦር አባላት በልዩ ልዩ ዘፈንና ወኔ በተሞላበት፣ በከፍተኛ የሐገር ፍቅር ስሜት ነበር የተቀበሉት። የዘመሩለትም።

አቤም ለሐገሩ ላስገኘው ክብር፣ ለራሱም ላስመዘገበው ክብረ-ወሰን ለሽልማት ግርማዊነታቸው ፊት ቀረበ። «ደጉ ንጉሣችንም» የምክትል አሥር አለቃነት የበታች ሹማምንቶች ማዕረግ አከናነቡት። አቤት ደግነት ይሉታል ይህ ነው¡

አበበ ቢቂላ በማራቶን ብቻም ሣይሆን በ5ሺህ፣ በ10ሺህ፣ በ21 ኪሎ ሜትር፣ በ12 ኪሎ ሜትር በሄደበት ሐገር ሁሉ ማሸነፍ ብቻም ሣይሆን ክብረ-ወሰንም ጭምር ነበር የሰበረው። አንድ መረሣት የሌለበት ጉዳይ ቢኖር አበበ በሮም ኦሊምፒክ ውድድር ካሸነፈ በኋላ ለጋዜጠኞች በሰጠው ቃለ-ምልልስ ላይ የተናገረው ነው። ይኸውም፣ «... እኔ የዛሬ ኦሊምፒክ አሸናፊ ከዓለምም አንደኛ ነኝ። በሐገሬ ላይ ግን ሁለተኛ ነኝ» ነበር ያለው። እንዴትና ለምን? ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ሲመልስም «እኔን የሚበልጠኝ ጓደኛ አለኝ። ይበልጠኛል። በውድድሩ ላይ ሣይሣተፍ የቀረውም በሰውነቱ ላይ ዘጠኝ ቦታ ቡግንጅ ወጥቶበት ነው። ስሙም ዋሚ ቢራቱ ይባላል። ስለዚህ ነው ብቻዬን የመጣሁት» ብሏል። የኢትዮጵያ ስፖርት ጋዜጠኞች ስለ ዋሚ ቢራቱ ያላሉት የለም። ሞራለ-ጠንካራውና «ዕድለ ቢሱ» ዋሚ ለኦሊምፒክ አይመረጥ እንጂ ከአበበና ከማሞ ወልዴ ጋር ብዙ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ተካፍሎ አሸንፏል። ከማሞና ከአበበ ጋርም ተከታትሎ ገብቷል። ዛሬ ዋሚ ቢራቱ በሕይወት የሚገኙ የ78 ዓመት አዛውንትና የ5 ልጆች አባት ናቸው። እኚህ እውቅ አትሌት የሐገራቱ ባለውለታ፣ በውድድር ዘመናቸው ፉክክር ሁሉ ለሐገሩ ክብር ማስገኘት ብቻ ስለነበር ምንም ዓይነት ቋሚ ንበረትና ሃብት አልነበራቸውም። ምሥጋና ይግባቸውና ዛሬ አቶ አላ-ሙዲ የተባሉ ባለቱጃር መኖሪያ ቤት አሠርተውላቸዋል።

የአበበ፣ የማሞና የዋሚ ታሪኮች የተያያዙ በመሆኑ በመሃከሉ ጀባ አልኳችሁ እንጂ የአበበ የውድድር ወይም የስፖርት ታሪኩን ለማየት ስንሞክር በርካታ ጥሎ ያለፋቸው አሻራዎች እንዳሉ እንገነዘባለን። ዓለም-አቀፍ ውድድሮች ላይ በአሸናፊዎች መድረክ ላይ ባንዲራችንን ማውለብለብ የቻለው አቤ ዳግም ሌላ ህልም ነበረው። የሚጨበጥ ራዕይ! በ1964 ላይ በጃፓን ሊደረግ ስለታሰበው የኦሊምፒክ ውድድር ላይ ለመሣተፍ ልምምዱን ጠዋትና ማታ ያካሔድ ነበር። በርካታ አበበዎችም አፍርቷል። ተከትለውታልም። በሮማ ኦሊምፒክ የልፋቱን ዋጋ ከሐገሩ መንግሥት በትክክል ባያገኝም የላቀ ክብር አግኝቷል። ሞራሉ የበለጠ ተጠናከረ። ክብሩንም ላለማስነካት ለቶኪዮው የኦሊምፒክ ውድድር ዝግጅቱን አጠናቀቀ።

የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ እያለ ስንክሣር አያጣምና አበበም ታሞ ሆስፒታል ገባ። ሁናቴው የኢትዮጵያን ሕዝብ ቢረብሸውም ፈጣሪ ምሥጋና ይግባውና! አቤ የቀዶ

ጥገና ሕክምና ተደርጐለት ወጣ። ወዲያውኑ ልምምዱን ጀመረ። ዝግጅቱንም አጠናቀቀ። ይሁን እንጂ አበበ ያሸንፍ ይሆን? የሚለው ጥያቄ በበርካታ የስፖርት አፍቃሪዎች ዘንድ አከራክሮ ነበር። ከሆስፒታል በወጣ በ36ኛ ቀኑ የኦሊምፒክ ውድድር እጩ የሆነው አትሌታችን ውድድሩን ለመካፈል ወደ ጃፓን ዋና ከተማ ወደ ቶኪዮ በረረ። በነገራችን ላይ ይህች ውብ ከተማ የተቆረቆረችው በወንዝ ላይ ነው።

አበበ ቶኪዮ ዓየር ማረፊያ ሲደርስ በከዘራ ተደግፎ ነበር። በዚህም ምክንያት ምዕራባውያን ጋዜጠኞችና ተችዎች ኢትዮጵያ እንደማታሸንፍ በሰፊው አናፈሱ።

ከዚያ ቀደም ሲል የአበበን ሁናቴ በቅርብ ሆነው ይከታተሉ የነበሩ የዓለም ጋዜጠኞች እሱ ወደታከመበት ሆስፒታል ድረስ በመሄድ አጨናንቀውት ነበር። ውድድሩ እስኪደርስ ድረስ አበበ በተደጋጋሚ ቃለ-ምልልሶችን አድርጓል። ለቀረበለት ጥያቄ ሁሉ «አትጨነቁ፤ አሸንፋለሁ።» በማለት ነበር በሙሉ ልብ የሚመልስላቸው የነበረ።

ጀግናው በቶኪዮ ለመሮጥ ያሰበው በጫማ ነው። ቶኪዮ በልዩ ልዩ ኅብረ-ቀለማትና በኦሊምፒክ ዓርማ አሸብርቃለች። የዓለም ሕዝብ በጉጉት ይጠብቀው የነበረው የኦሊምፒክ መዝጊያ ውድድርም እልህ አስጨራሽና ወኔንና ጉልበትን የሚጠይቅ ነበር። ውድድሩ እንደተጀመረ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ተወዳዳሪዎች አንዱን ከአንዱ በማይለይበት ሁናቴ ማፊትለክ ጀመሩ። ቢሆንም ከመጀመሪያው አንስቶ የመሪነቱን ቦታ አበበ ብቻውን ተያይዞታል። እናም ቃሉን አላጠፈም። ዳግም የኦሊምፒክ ክብረ-ወሰን በመስበር ድልን ተቀዳጀ። በሮም ከተማ የሰበረውን ሰዓት በ2፡12፡15 አሻሻለው። ዓለም ዳግመኛ ጉድ አለ!። የማይደገመው ተደገመ፤ ተደግሞ የማያውቀው የማራቶን ድል ተደገመ። ለአቤም እንዲህ ሲባል ተቀኘለት፤

ሮምን በባዶ እግሩ፤ ቶኪዮን በጫማ

ድል አድርጓል አቤ በሁለቱም ከተማ

ይህ ድንቅ አትሌታችን ክብሩን ጠብቆ፤ ታሪኩን ደግሞ፤ የሐገሩንም ሰንደቅ-ዓላማ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ አደረገ። በዓለም ዙሪያ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆነ። እስከዛሬም ድረስ ቢሆን የዓለም ሕዝብ አበበን ጠንቅቆ ያውቀዋል።

ይህንኑ አንፀባራቂ ድል አንድ በስዊስ የሚታተም ጋዜጣ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፤

' ' ...Des 1960, le marathon olympique n'est plus l'apanage des Européens et des Américains. Un homme, descendu des hauts plateaux éthiopiens, crés la sensation dans le crépuscule romain. Cet inconnu s'appelle Abebe Bikila. Il court pieds nus. Quatre ans plus tard, mais avec des chaussures, il l'emporte de nouveau à Tokyo.' '

*«ከ1960 ጀምሮ የኦሊምፒክ ማራቶን የአውሮጳውያንና የአሜሪካውያን የግል ሃብት መሆኑ አበቃ። ከኢትዮጵያ ደጋዎች የተወለደ አንድ ሰው የሮማን የንጋት ውጋጋን ስሜት ፈጠረ። ይህ ያልታወቀ ሰው አበበ ቢቂላ ይባላል። ባዶ እግሩን ይሮጣል። ከአራት ዓመት በኋላ፤ ግን ጫማ አጥልቆ በድጋሚ ቶኪዮ ያሸንፋል።»*

ለአፍሪቃ፤ ለጥቁር ሕዝቦችና ለኢትዮጵያም የስፖርት በር ከፋችና ምሣሌ በመሆን ጀግናው አበበ በቶኪዮ ዳግም ድል አድርጎ ወደ ሐገሩ ተመለሰ። ከፍተኛ የክብር

አቀባባልም ተደረገለት። ለእናት ሐገሩ ባለውለታነቱና ለራሱም ላጐናፀፈው ክብር፣ የልፋቱን ዋጋ ከሐገሩ መንግሥት ለማግኘት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፊት ለሁለተኛ ጊዜ ቀርቦ የምክትል የመቶ አለቃነት ማዕረግ ሹመት ተቀበለ። የማራቶን ጀግናነቱንም አረጋገጠ።

ቀጣዩ ኦሊምፒክ ለአበበም ሆነ ለኢትዮጵያ በጣም አስፈለጊ ብቻም ሣይሆን ታሪካዊነቱም የላቀ እንደሚሆን ግንዛቤ እየያዘ መጣ። ቀጣዩ የኦሊምፒክ ውድድር ሊደረግ የታሰበው ከአራት ዓመታት በኋላ ሜክሲኮ ላይ ነው። ለአበበም ሆነ ለተከታዮቹ የሚታያቸው ራዕይ ከውድድሩ በስተጀርባ ያለው ቁም ነገር ብቻ ነው። በተከታታይ ለሦስት ጊዜ ማሸነፍ ከቻሉ የማራቶን ንጉሥ የሚለው ክብር ማግኘት ነበር ለጥንካሬያቸው ተጨማሪ ግፊት። በነገራችን ላይ ለሦስት ጊዜ የኦሎምፒክ ማራቶንን በመከታተል ያሸነፈ እስከዛሬ የለም። ጀርመናዊው ሯጭ እንዲሁ እንደ አበበ ሁለት ኦሊምፒኮችን ብቻ ነበር በተከታታይ ያሸነፈው። እንደ ሕይወቴ ሩጫን እወዳለሁ። ሕይወቴም ሩጫ ናት (running is my life) ነበር ያለው። አበበ ብዙዎች አበበዎችን አፍርቷል። ብቻውን አይደለም። ማሞ ወልዴም ከኮሪያ ዘመቻ በድል ተመልሷል። ዋሚ ቢራቱ፣ ባሻ ፍቅሩ፣ በየነ አያኖም፣ የትነበርክ በለጠ፣ ሽብሩ ረጋሣ... እነዚህ ሁሉ ከአበበ የማይተናነሱ የዘመኑ ፈጣኖች ነበሩ። ቢሆንም የኢትዮጵያ ችግር «ምንጊዜም» አይጠፋምና በበጀት ምክንያት ሁሉም አይሄዱም። የምርጦች ምርጥ ይመረጣል። በ1968 የሜክሲኮ ኦሊምፒክ የምርጦች ምርጥ አበበና ማሞ በመሆን ተመረጡ። ጊዜው ሲደርስም ጉዞው ወደ ሜክሲኮ ሆነ፣ ከበዙ ሰዓት የዓየር በረራ በኋላ ሜክሲኮ ሲቲ ሲገቡ የኢትዮጵያም ሆነ የዓለም ጋዜጦች ርዕሰ አንቀጽ ገፆችን አበበና ማሞ ሸፈኑት።

ሁለቱም ምርጥ አትሌቶቻችን በአካልም በመንፈሰም ተዘጋጅተዋል። አበበ የኦሊምፒክ የማራቶን ንጉሥ ለመባል፣ ማሞም በበኩሉ የመጀመሪያ ውጤት%ን ለማየት!። በሜክሲኮ ጥቂት ቀናት ቆይታቸውም ከአካባቢው ዓየር ጋር ለመተዋወቅ የልምምድ ፕሮግራምም ነበራቸው፣ በቀረው ትርፍ ጊዜያቸው ደግሞ ልዩ ልዩ ታሪካዊና መዝናኛ ቦታዎችን በመጐብኘት አሣለፉ።

አይደርስ አይቀር የውድድሩ ቀን ደረሰ። ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ጋር በመሆን የማስነሻውን ጥይት ተኩስ ይጠባበቃሉ፣ ውድድሩ ከተጀመረ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ጀግኖቹን አበበንና ማሞን የሚፎካከራቸው ጠፋ፣ የዕለቱ ዓየር ጠባይም ፀሃያማና ተስማሚ ስለነበር ተራ በተራ የመሪነቱን ቦታ ይቀባበላሉ። የውድድሩን ሂደት የሚከታተለውና የሚያስተላልፈው የሜክሲኮ ሬዲዩም ያለምንም ማጋነን የሁለቱን ኢትዮጵያውያን በተለይም ደግሞ የአበበን ታሪክ አስመልክቶ ነበር ልዩ ትኩረት የሰጠው። ማሞንም በሚመለከት ከአራት ቀናት በፊት በ10ሺህ ሜትር የብር ሜዳሊያ ባለቤት የመሆኑን ታሪክ በሰፊው ያትታል፣ ውድድሩን በየተራ ለብቻቸው ይቀባበሉ ስለነበር ማን ያሸንፍ ይሆን? የሚል ጥያቄ መነሣቱ አልቀረም። ይሁንና ሁለቱም አትሌቶቻችን ከባዱን ጐዳና ተያይዘውታል። የውድድሩን የመጀመሪያ 25 ኪሎ ሜትር አገባደውታል።

በመሀሉ ማሞ ባልገመተውና ባላሰበው ሰዓት በጆሮው ተምዘግዝጐ የገባውን የአበበን ቃላት ማመን አቃተው። እንደመደንገጥ ብሎ «ምን አልከኝ?» በማለት ጠየቀው። አበበም የማሞን መደናገጥ ስለተገነዘበ እንደ ማባበል ዓይነት አለና «አይዞህ ታሸንፋለህ፣ እኔ አልቻልኩም፣ የእግሬ ወለምታ በጣም ተሰምቶኛል፣ ሌላም የማላውቀው ስሜት እየተሰማኝ ነው። ስለዚህ አደራዬን ተቀበለኝ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይጠብቀናል፣ እኔ ስላልቻልኩ አንተ ቀጥል፣ የኢትዮጵያ አምላክ ይከተልህ» ካለው በኋላ አስፋልት ዳር ወደቀ። እውነትም

በጣም ታሟል። ወዲያውኑ አበበ ሜክሲኮ ሆስፒታል በአስቸኳይ ተወሰደ። ማራቶን ልዕልቷ አቤን ከዳችው።

እርግጥ ነው በዚህ ውድድር የተጠበቀው አበበ ቢቂላ ነበር። የአበበ ውድድሩን ማቋረጥ ብዙዎቹን በማስደንገጡ በስቴዲየሙ የተገኙ ኢትዮጵያውያኖች የአበበ ማቋረጥ እንደተሰማ ስቴዲየሙን ለቀው ማሞ ወልዴን ለማበረታታት ወደ አደባባይ ወጡ። በዚያን ወቅት የነበረውን ሁናቴ ታዋቂው ጋዜጠኛ ሰለሞን ተሰማ እንዲህ ገልፆት ነበር፤

«የአበበን መውጣት ስሰማ ማሞን ለማበረታታት የጮህኩት ጩኸት ድምፄን ለሦስት ቀናት ያህል ዘግቶት ነበር።»

ማሞ ብቻውን ቀሪውን ኪሎ ሜትር እየመተረ፣ በከፍተኛ ሞራል በመገስገስ ያለተቀናቃኝ የሜክሲኮን ኦሎምፒክ አሸንፎ የወርቅና የብር ሜዳሊያ ባለቤት ሆነ። ማሞ በዚህ የሜክሲኮ ውድድር የ10 ሺህ ኪሎ ሜትር ማጣሪያና ፍፃሜ ውድድርን ጨምሮ 62 ኪሎ ሜትር ከ195 ሜትር በመሮጥ የአንድ የወርቅና የአንድ ነሐስ ባለቤት በመሆን ብቸኛው ኢትዮጵያዊ ሣይሆን አይቀርም።

አበበ ከሆስፒታል ወጥቶ ማሞን ባየ ጊዜ እጅግ ከመደሰቱም በላይ ስቅስቅ ብሎ ካንጀቱ አለቀሰ። «የኢትዮጵያ ሕዝብ ይጠብቀናል» ብሎት ስለነበር ማሞ አላሣፈረውም። በሦስት ተከታታይ የማራቶን ውድድሮች ኢትዮጵያ የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት በመሆኗ ዓለምን ቢያስደንቅም የኢትዮጵያ ሕዝብ ደስታው ከመጠን በላይ ሆኗል። የቡድኑ አባላት ወደ አዲስ አበባ የተመለሱ ዕለትም አበበንና ማሞን ለመቀበል ሕዝቡ በነቂስ ነቅሎ ወጥቷል። ዕልልታው፣ ዘፈኑ፣ ዝማሬው፣ ጭፈራው የአዲስ አበባ ጐዳናዎችን ከማስጨነቁም ባላይ አዲስ አበባ ከመመሰቃቀሏ የተነሣ የሠርግና የደስታ አውድማ መስላለች። የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በየአግጣጫው ይውለበለባል። የክብር ዘበኛው ባንድ ጀግኖቹን ለመቀበል በልዩና በሚያስደስት ቅንብር ያሣየው ትርዒት ድንቅ ነበር። እንዲህ ነው ጀግንነት! እንዲህ ነው ወንድነት! አበበና ማሞ አንድና ሁለት! በማለት እንዲህ ሲባል ተገጠመላቸው፤

ማራቶን ማራቶን ማራቶን ውዲቷ

አበበና ማሞ ሆነዋል ባለቤቷ

ማራቶን ጠብቀሽ አቤን ብትቆጪ

ሆኖም አልቀረልሽ የትም አታመልጪ

አበበ ቢወጣ በእግር ወለምታ

ማሞ ተተክቷል የሐገሩ መከታ

ሮምን በባዶ እግሩ ቶኪዮን በጫማ

ድል አድርጓል አቤ በሁለቱም ከተማ

ተባለላቸው፣ ተዘመረላቸው። ተጨፈረላቸውም።

አበበ እንደ ዛሬ የዘመኑ ሥልጣኔ ባልተስፋፋበት ጊዜ በባዶ እግሩም፣ በጫማም የኦሊምፒክ ውድድርን ብቻ ሣይሆን በተለያዩ ውድድሮች አሸንፏል። ከዋሚና ከማሞ

ጋርም ብዙ የዓለም-አቀፍ ውድድሮች ላይ ተካፍለው አሸንፈዋል። በዚያን ጊዜ አበበ የገባበት ሰዓት ዛሬም ቢሆን በቀላል አይገባም።

አበበ ቁመቱ ሎጋ፣ የቀይ ዳማና መልከ-መልካም ኢትዮጵያዊ ነበር። በመልኩና በቁመናው እንዲሁም ባስመዘገበው ውጤት በመላው ዓለም ትልቅ ስምና ክብር አግኝቷል።

ከዚህ ውድድር በኋላ የጀግናው ሕይወት እንዴት ነበር የሚል ጥያቄ አንባቢያን ሊሰነዝሩ ይችላሉ። አበበ የጀግንነት ክብር ማግኘቱ፣ ዝናና ታዋቂነት ማትረፉ፣ በአጠቃላይም ስሙ በሐገር ውስጥም ይሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ ጎልቶ ይታወቅ እንጂ በሕይወት ዘመኑ በርካታ ፈተናዎች ውስጥ ገብቷል። ዝነኛ ሰው ብዙ ችግሮች አጋጥመውታል። ቅናት እና ፍቅር ዋነኛዎቹ ናቸው። አበበም ከሁለቱ ለማምለጥ አልቻለም። ጀግና ይወደዳል፣ ይፈቀራል፣ ይከበራል።

በ1972 ዓ.ም. በጀርመን ሙኒክ ከተማ የተካሄደው የማራቶን ውድድር ለኢትዮጵያውያኖች የመጨረሻ ድል ነበር። አበበ ቢቂላ በሙኒክ ከተማ የተገኘው እነዚያ የሚወናጨፉ እግሮቹን አጣጥፎ፣ በተሽከርካሪ ወንበር ላይ [1] ሲሆን፣ በስታዲየሙ የተገኙ ተመልካቾች ከመቀመጫቸው ተነስተው በጭብጨባ ነበር ተቀበሉት።


በዚሁ በሙኒክ ውድድር በአርባ ዓመት ዕድሜው የተሣተፈው ማሞ 2:14:31 በመግባት 3ኛ ወጥቶ የነሐስ ሜዳሊያ ተሸላሚ ለመሆን በቃ። [2] በነገራችን ላይ በሙኒኩ ውድድር ኢትዮጵያ በማራቶን ነሐስ ሜዳሊያ ከማግኘቷ ሌላ በ10ሺህ ኪሎ ሜትር በአትሌት ምሩፅ ይፍጠር አማካይነት ሁለተኛውን ነሐስ አግኝታለች።

ጀግናው አበበ ቢቂላ በተሽከርካሪ ወንበር ላይም ሆኖ በድጋሚ የዓለም የቀስት ሻምፒዮን ሆኗል። በእግሩ ያጣውን የወርቅ ሜዳሊያ በዓይኖቹና በእጆቹ ለማግኘት ችሏል።

በ1966 ዓ.ም. አቤ ለዘላለም ይለየን እንጂ። ሻምበሉ ምን ጊዜም ሕያው ነው። ስሙ ከመቃብር በላይ ነው። አበበ ዛሬም ለሚሊዮን ኢትዮጵያውንና ሌሎች አትሌቶች አርዓያና የ«Inspiration» ምንጭ በመሆን በርካታ አበበዎችን ተክቶልን አልፏል።

የዚህ ዕውቅና ድንቅ አትሌታችን የክብር መታሰቢያ ሐውልት በባዕድ ሐገር በቶኪዮ በክብር ከመቆሙም በላይ ልዩ እንክብካቤም እንደሚደረግለት አንባቢያን እንዲገነዘቡልኝ እሻለሁ። በሐገራችን ያለው የአበበ ሐውልት ጉዳይ ግን እጅግ አሣዛኝ ነው። አቶ አቤ ሴሎም በክብር ያሠሩለት ሐውልት ዛሬ ምን እንደሚመስል ለአንባቢያን እተዋለሁ።

በመጨረሻም ኢትዮጵያ ከ1972 ዓ.ም. በኋላ ለማራቶን ድል ባትታደልም በተሣተፈችባቸው ኦሊምፒኮች ሁሉ የሩጫን ድል አላጣችም። በ10ሺህና በ5ሺህ ኪሎ ሜትር ውድድሮች ብርቱ አትሌቶች ድል አጎናፅፈውታል። ምሩፅ ይፍጠር፣ መሐመድ ከድርና ቶሎሣ ቆቱ በ10ሺህ፣ መሐመድ ከድር፣ ዮሐንስ፣ ምሩፅ ይፍጠርና እሸቱ ቱራ የቡድን ሥራ በመሥራት በ5ሺህ ኪሎ ሜትር ተከታትለው በመግባት ሞስኮ ላይ ታሪክ ሠርተዋል።



ኢትዮጵያን ያስጠሩ እግሮች

ኢትዮጵያ በ1992 ዓ.ም. በስፔን ባርሴሎና በተካሄደው ውድድር በደራርቱ ቱሉ በ10ሺህ፤ በፊጣ ባይሣና በአዲሱ አበበ 1የወርቅና 2 የነሐስ አግኝታለች።1996 ዓ.ም. በአትላንታ ኦሊምፒክ ኃይሌ ገ/ስላሴ፤ ጌጤና ፋጡማ ሮባ በድል አንበሽብሸውናል። ንጉሱ በንግሥት ተተካ። በአትላንታ።አበበ የባረከውን፤ ማሞ የደገመውን የማራቶን ድል አትሌት ፋጡማ ሮባ አፀናችው። ኢትዮጵያ በወንዶች ብቻ ሣይሆን በሴቶች ማራቶን እንደገና ንግሥት ሆና ብቅ አለች። በአበበ ቢቂላ ፈር ቀዳጅነት ጥቁር ሕዝቦችን ያኮራው የማራቶን ድል በማሞ ወልዴ አርማ አንሺነት የፀደቀው የማራቶን ድል፤ ዛሬ ከማንም በላይ ለኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊያት ሁሉ ተናፋቂ ነው።

በሚቀጥለው ተረኛ ባለታሪክ እስከምንገናኝ ድረስ ቸር ይግጠመን።

<u>የግርጌ ማስታወሻዎች፤</u>

(1) በዘመኑ በኢትዮጵያ ራዲዮ እንደተነገረው አበበ ሸኖ በምትባል አካባቢ መኪና ተገልብጦ አደጋ ደረሰበት የሚል ዜና ተሠራጨ። በእውነት አበበ የሚኪና አደጋ ነው የደረሰበት? እንዴት ሁለቱን ፈጣን እግሮቹን ብቻ አደጋ ደረሰባቸው? ዓይኑ አልተነካ፤ እጁ ላይ ቁስል አልደረሰበት። ምንድነው ምስጢሩ? እስካሁን ድረስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የአበበ አሟሟት ትክክለኛ መንስዔ በትክክል ካለመታወቁም ባለይ እንቆቅልሽም ሆኖ ይገኛል። የአሟሟቱ መንስዔ የተሣፈረባት ቮልስቫገን ሣትሆን «ልዩ እጅ» የነበረው ስለመሆኑ በጊዜው ልንሰማ ችለናል።

(2) ይህንን የመጨረሻ ድል ያስገኘልን ብርቅ አትሌት ማሞ ወልዴ «በዘር ማጥፋት» ወንጀል ተከሶ በእሥር ቤት ይማቅቃል። ኢህአዴግ በዓለም አቀፍ በኦሎምፒክ መንደር ታላቅ ገድል ሰርቶ የሐገር ባለውለታ የሆነውን ማሞን ወልዴን በአትላንታ ከዚያም በኋላ በሲዲኒው ኦሊምፒክ መከፈት አስመልክቶ ከእስር ሊፈታው በተገባ ነበር።